# የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ ለመከላል እና ለመቆጣጠር የተመደበ ፈንድ የሚመራበት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት

## መመሪያ ቁጥር 247/2013

**የገንዘብ ሚኒስቴር**

**ሚያዝያ/2012 ዓ/ም**

# የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ ለመከላል እና ለመቆጣጠር የተመደበ ፈንድ የሚመራበት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት

## መመሪያ ቁጥር 247/2013

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አውጪው ባለሥልጣን**

   የኢ.ፌ.ድ.ሪ የገንዘብ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 31 እና 75 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ መመሪያ ‹‹የኮሮና ቫይረስ (COVID -19) ወረርሽኝ ለመከላል እና ለመቆጣጠር ከአገር ውስጥና እና ከውጭ የተገኘ ፈንድ የሚመራበት የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 247/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

   3.1. **ፈንድ፡-** በዚህ መመሪያ ዉስጥ ፈንድ ተብሎ የተጠቀሰው የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ለመከላከልና ለመቆጣጠር የተሰበሰበ ገንዘብ እና ንብረት ማለት ነው፡፡

   3.2. **አላቂ ዕቃ፡-** የንጽህና መጠበቂያ ዕቃዎች፣ ኬሚካሎች፣ መድኃኒቶች፣ አልባሳቶች፣ ፍራሾች፣ የምግብ፣ ሸቀጣሸቀጦች እና የመሣሰሉትን ያካትታል፡፡

   3.3. **ጥሬ ገንዘብ፡-** በባንክ እና በሳጥን የሚቀመጥ ጥሬ ገንዘብ ማለት ነው፡፡

   3.4. **በጊዜያዊነት የሚያዝ አደራ ንብረት፡-** ለወረርሽኙ መከላከል በጊዛያዊነት የሚሰጥ ቤቶች፣ ተሽከርካሪዎች፣ ማሽነሪዎችን እና የመሳሳሉትን ንብረቶችን ያካትታል፡፡

   3.5. ወረርሽኝ፡- የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ማለት ነው፡፡

   3.6. ብሔራዊ ኮሚቴ፡- የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ለመከላከልና ለመቆጣጠር በፌዴራል ደረጃ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተቋቋመ ኮሚቴ ማለት ነው፡፡

3.7. "ቋሚ ንብረት" ማለት በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 የተሰጠውን ትርጉም የሚይዝ ሆኖ የተናጠል ዋጋው ከብር 1000 /አንድ ሺህ/ እና ከዚያ በላይ የሆነ ንብረት ነው፡፡

4. **የመመሪያው ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የኮረና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰበውን ገቢ እንዲያስተዳድሩ በፌዴራል ደረጃ ኃላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

5. **ዓላማ**

የዚህ መመሪያ ዓላማ የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከውጭ እና ከአገር ውስጥ የሚኘውን የእርዳታ ገንዘብና ንብረት አሰባሰብ፣ አስተዳደር፣ ክፍያ አፈፃፀም፣ ሪፖርት አቀራረብ እና የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ወጥ በሆነ ሁኔታ እንዲሰራ በማድረግ ፈንዱ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል ማድረግ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ተግባርና ኃላፊነት

6. **የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት**

6.1. የባንክ ሂሳብ በሁሉም ባንኮች ይከፍታል፣ ዕርዳታ ወይም ድጋፍ ለሚያደርጉት አካላት ያሳውቃል፣

6.2. ዕርዳታውን ወይም ድጋፉን በጥሬ ገንዘብ ለሚያደርጉት አካላት ደረሰኝ የሚፈልጉ ከሆነ ገቢ መደረጉን አረጋግጦ ማስረጃ ይሰጣል፤

6.3. በግል ባንኮች አማካይነት የተሰበሰበው የዕርዳታ ገንዘብ ለዚሁ አገልግሎት ወደ ተከፈተው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ሒሳብ በየቀኑ መተላለፉን ይከታተላል፣

6.4. ብሔራዊ ኮሚቴው በሚሰጠው አመራር መሰረት ገንዘቡ ለተፈቀደላቸው የፌዴራል አስፈጻሚ መ/ቤቶች ያስተላልፋል፣የሂሣብ ሪፖርት በየሶስት ወሩ እየተዘጋጀ መቅረቡን ይከታተላል፣

6.5. ለፈንዱ አገልግሎት የሚውሉ የፋይናንስ ሠነዶችን በመመሪያው መሠረት እንዲተላለፉ ያደርጋል፣ ተፈጻሚነታቸውን ይከታተላል፣እንዲሁም በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈጸሙ ዝርዝር የግዥ፣ የበጀት ፣ የንብረት አጠቃቀሞችን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

6.6. ወረርሽኙ ከቆመ በኋላ ለዚህ ሥራ የተገዙ ወይም በዕርዳታ የተገኙ ንብረቶችን ለተቋማት ይመድባል፤ ጥሬ ገንዘቡን ወደ ተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ ገቢ ያስደርጋል፤ ተገቢው ምዝገባ መካሄዱንም ይከታተላል፤

## 7. የፌዴራል አስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

7.1. በCOVID-19 ወረርሽን ምክንያት መንግስት ከሰጣቸው ተልኮ አንጻር ወረርሽኙን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስፈልጋቸውን በጀት ድጋፍ ለብሔራዊ ኮሚቴው ያቀርባሉ፤ በብሔራዊ ኮሚቴው የተፈቀደውን በጀት ለተፈቀደላቸው ዓላማ ብቻ መዋሉን ያረጋግጣሉ፤

7.2. ብሔራዊ ኮሚቴው በሚሰጠው አመራር መሰረት የተመደበውን ገንዘብ ከገንዘብ ሚኒስቴር በመቀበል ለየወረርሽኙን የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ ያውላሉ ፣የሂሣብ ሪፖርቱን በየሶስት ወሩ እያዘጋጁ ያቀርባሉ፣

7.3. በወረርሽኙ የመከላከል ዘመቻ ለሚሳተፉ የጤና ባለሙያዎች እና ሌሎች ባለሙያዎች በጤና ሚኒስቴር እና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን በጋራ ተዘጋጅቶ በመንግስት በሚፀድቀው የጥቅማጥቅም መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፤

7.4. ወረርሽኙ ከቆመ በኋላ ለዚህ ጉዳይ የተገዙና በዕርዳታ የተገኙ ንብረቶችን በዝርዝር መዝግበው ለገንዘብ ሚኒስቴር ያስተላልፋሉ፤

7.5. አስፈጻሚ አካላት በወረርሽኙ ምክንየት የተላለፈለቸውን ገንዘብ በብሔራዊ ኮሚቴው ጸድቆ በገንዘብ ሚኒስቴር ካልተረጋገጠ በስተቀር ለሌላ ስራ በፍጹም ማዋል አይችሉም፤

## 8. የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ተግባርና ኃላፊነት

8.1. በክልል ደረጃ ወረርሽኙን ለመከላል እና ለመቆጣጠር የሚሰበሰበው ገቢ በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል የፌዴራል መንግስት ወረርሽኙን ለመከላል እና ለመቆጣጠር ያወጣውን የፈንድ አስተዳደር መመሪያ በመከተል የክልሉ ፈንድ የሚመራበት የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ ያዘጋጃሉ፤

8.2. ከፌዴራል መንግስት በገንዘብ ሚኒስቴር ወይም በፌዴራል አስፈጻሚ አካለት በኩል ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ወረርሽኙን ለመከላል እና ለመቆጣጠር የሚተላለፈውን ፈንድ አጠቃቀም በተመለከተ ሪፖርት ያቀርባሉ፤

8.3. ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት በኩል ወረርሽኑን ለመከላል እና ለመቆጣጠር የሚሰበሰበው ገቢና የፈንዱ አጠቃቀም በተመለከተ ለብሔራዊ ኮሚቴና ለገንዘብ ሚኒስቴር የተጠቃለለ ሪፖርት በየጊዜው ያቀርባሉ፤

## 9. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተግባርና ኃላፊነት

9.1. ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚተላለፍ ቋሚ ትዕዛዝ መሠረት ለወረርሽኙ መከላከያ በተከፈቱ የባንክ ሂሳቦች ገቢ የተደረጉ ገንዘቦች በየዕለቱ 11:00 ሰዓት ላይ በኢት/ብሔራዊ ባንክ ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ መከላከያና መቆጣጠሪያ ተብሎ ወደ ተከፈተው የባንክ ሂሳብ ያስተላልፋሉ፤

9.2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባንክ በባንክ ሂሳቡ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ ክሬዲት አዲቫይስ ለገንዘብ ሚኒስቴር ይልካሉ፤

9.3. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ መከላከያና መቆጣጠሪያ ተብሎ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ የተደረገውን ገንዘብ በገንዘብ ሚኒስቴር የበላይ ኃላፊዎች የባንክ ሂሳቡን እንዲያንቀሳቅሱ ውክልና በተሰጣቸው ሰዎች ብቻ ይንቀሳቀሳል፤

9.4. ገንዘብ ሚኒስተር የክፍያ ሥርዓቱን ሊያቀላጥፍለት የሚችሉ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መደቡ A የሆነ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈትና ወጪዎችን ከዚሁ የባንክ ሂሳብ እንዲንቀሳቀስ ያደርጋል፤

## 10. የግል ንግድ ባንኮች ተግባርና ኃላፊነት

10.1. ከገንዘብ ሚኒስቴር በሚሰጠው ቋሚ ትዕዛዝ መሠረት ለወረርሽኙ መከላከያ በተከፈቱ የባንክ ሂሳቦች ገቢ የተደረገውን ገንዘብ በየዕለቱ በ11:00 ሰዓት በኢት/ብሔራዊ ባንክ ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ መከላከያና መቆጣጠሪያ ተብሎ ወደ ተከፈተው የባንክ ሂሳብ ያስተላልፋሉ፤

10.2. የግል ንግድ ባንኮች የፈንዱን ገቢ ሰብስበው ወደ ብሄራዊ ባንክ ከማስተላለፍ ውጭ ከተሰበሰበው ገንዘብ ላይ ለሌላ አካል አያስተላልፉም ወይም አይከፍሉም፤

10.3. የግል ንግድ ባንኮች ላስገቢው አካላት የክሬዲት አድቨይስ መስጠት አለባቸው፤

10.4. የግል ንግድ ባንኮች ለኮቢድ-19 የባንክ ሂሳብ መክፈት የሚችሉት የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያስተላልፍላቸዉ ትዕዛዝ ብቻ ነው፤

## ክፍል ሶስት

## ፈንድ አሰባሰብ እና አስተዳደር

### 11. ስለ ፈንድ አሰባሰብ እና አስተዳደር

11.1. የገቢ ዓይነቶች፡-

ሀ. በጥሬ ገንዘብ የሚሰበሰብ ገቢ፣

ለ. በዓይነት የሚገኝ አላቂ እና ቋሚ ዕቃ፣

ሐ. በጊዚዊነት በአደራ የሚሰጥ ንብረት፣

መ. የትራንስፖርት አገልግሎት፣

ሰ. ሌሎች፣

11.2. የገቢ ምንጭ

ሀ. ከመንግስት የሚመደብ ገንዘብ፣

ለ. ከመንግስትልማት ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍ፣

ሐ. ከግል ድርጅቶች የሚሰጥ ድጋፍ፣

መ. መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት (NGO) የሚገኝ ድጋፍ፣

ሠ. ከመንግስትና ከግል ተቀጣሪ ሰራተኞች የሚሰበስብ ገቢ፣

ረ. ከኃይማኖት ተቋማት የሚገኝ ድጋፍ፣

ሰ. ከግለሰቦች የሚሰጥ ድጋፍ፣

ሸ. ከዲያስፖራ የሚገኝ ድጋፍ፣

ቀ. ከውጭ መንግስታትና ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚገኝ ዕርዳታ፣

በ. ሌሎች

### 12.የጥሬ ገንዘብ አሰባሰብ

12.1. በውጭ ምንዛሬ የሚገባ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ መከላከያ ተብሎ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ ይደረጋል፤

12.2. የጥሬ ገንዘብ አሰባሰብ በባንክ ዝውውር፣ በቼክ ወይም በጥሬ ገንዘብ ሊሆን ይችላል፤

12.3. ከአገር ዉስጥ በኢትዮጵያ ብር ተሰብስቦ በባንክ ገቢ የሚደረገው ጥሬ ገንዘብ ወይም ቼክ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና በግል ንግድ ባንኮች ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) ወረርሽኝ መከላከያ ተብሎ በተከፈቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥሮች ገቢ ይደረጋል፤

12.4. ከመንግስት ሠራተኞች፣ ከግል ድርጅት ሠራተኞች እና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ሠራተኞች የሚሰበሰብ ገቢ ፔይሮሉን በሚያዘጋጀው መስሪያ ቤት አማካይነት የተሰበሰበው ገንዘብ በየወሩ መጨረሻ ቃል የተገባው እስኪጠናቀቅ ሳይቋረጥ በመንግስት ወይም በግል የንግድ ባንኮች ለዚሁ አገልግሎት በተከፈቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ይደረጋል፤

12.5. በገንዘብ ያዥ ወይም  ገቢ እንዲሰበስብ ውክልና የተሰጠው አካል አማካይነት በጥሬ ገንዘብ የሚሰበሰብ ገቢ በየዕለቱ ለዚሁ አገልግሎት በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ አለበት፤

12.6. ባንክ ገቢ ለሚደረጉ ገንዘቦች የባንክ ገቢ አድቫይስ እንደ ደረሰኝ ይቆጠራል፤

## 13. የጥሬ ገንዘብ መሰብሰቢያ ገቢ ደረሰኞች እና አመዘጋገብ

13.1. የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች በባንክ ለሚያስገቡት ገቢ ከባንክ የሚሰጣቸው አድቫይስ ወይም ስሊፕ እንደገቢ ደረሰኝ ተጠቅመው የሂሳብ ማስመስከሪያ ቫውቸር በመጠቀም የሂሳብ ምዝገባ ያከናውናሉ፤

13.2. ገንዘብ ሚኒስቴር በየዕለቱ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የባንክ ስቴትመንት እና አድቫይሶችን በመሰብሰብ ከየትኛው ባንክ እንደገባ በእያንዳንዱ ገቢ አድራጊ ባንክ የገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት ይመዘግባል፤

13.3. የጥሬ ገንዘብ ገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተለየ ማሳተም ሳያስፈልግ ለመደበኛው ሥራ ከገንዘብ ሚኒስቴር ገዝተው ወይም በገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ አሳትመዉ የሚጠቀሙ መስሪያ ቤቶች ከሚጠቀሙበት ውስጥ የተወሰኑ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ፓዶችን በመለየት ለዚሁ ተግባር ብቻ እንዲውል በማድረግ ይጠቀማሉ፤

13.4. መስሪያ ቤቶች ለወረርሽኙ መከላከያና መቆጣጠሪያ የሰበሰቡትን ገቢ ወደ ባንክ ከማስገባት ውጭ ወጪ አድርገው መጠቀም አይችሉም፤

13.5. የአገር ውስጥ እርዳታ ገቢ በገቢ ሂሳብ ኮድ 1483 የሚመዘገብ ይሆናል፤

13.6. ከዲያስፖራ የሚገኝ እርዳታ በገቢ ሂሳብ ኮድ 1489 ይመዘገባል፤

14. **በዓይነት የሚሰበሰብ ገቢ**

14.1. የአላቂ ዕቃዎች ፣የንጽህና መጠበቂያ፣ መድኃኒቶች፣ ምግብ፣ ጥሬ ዕቃዎች እና ሸቀጣ ሸቀጦች፣ አልባሳት እና ሌሎች አላቂ ቁሳቁሶች የወቅታዊ የገበያ ተመን ተወስዶ ለዚሁ አገልግሎት በተለየው የንብረት ገቢ እና ወጪ ደረሰኞች እየተመዘገበና ወጪ እየተደረገ ለፈንዱ ቁጥጥር ስራ ይውላል፡፡

14.2. በጊዛያዊነት የሚሰጡ አደራ ንብረቶች

ሀ. በጊዚያዊነት የሚሰጡ ሕንፃዎች፣ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ቋሚ ዕቃዎች የተለየ ፎርም ተዘጋጅቶ በአደራ ይመዘግበል፤

ለ. በአደራ በመረከብ አገልግሎት እየዋለ በነበረበት ወቅት በንብረቱ ላይ የተለየ ጉዳት ቢደርስ፣ ዕቃ ቢሰበር እና ቢበላሽ በዕለቱ ይመዘገባል በመጨረሻም እንዲጠገንለት ዕርዳታ ሰጪው ቢጠይቅ በአገልግሎቱ ወቅት መበላሸቱ ከተረጋገጠ ሊጠገንለት ይችላል፤

14.3. ሙሉ በሙሉ በስጦታ የሚሰጡ ቋሚ ዕቃዎች በሚኖርበት ጊዜ፣

ሀ. በስጦታ የተሰጠዉ ዕቃ በፈቃደኝነት የተሰጠ እና ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ስለመሆኑ ባለንበረቱ በጽሑፍ ፈርሞ መስጠት አለበት፣

ለ. በስጦታ የተገኙ ቋሚ ንብረቶች ወረርሽኑ ሲያበቃ በገንዘብ ሚኒስተር በኩል ለመንግስት ተቋማት ሊደለደል ይችላል፤

## ክፍል ሦስት
## የበጀት እና የወጪ ሂሳብ አያያዝ

15. **የበጀት አያያዝ እና አመዘጋገብ**

15.1. ከአገር ውስጥ ዕርዳታ የሚሰበሰብ ገቢ በገቢ ሂሳብ ኮድ 1483 እንዲሁም ከዲያስፖራ የሚገኝ ዕርዳታ በገቢ ሂሳብ መደብ 1489 በመመዝገብ ከዚሁ የሚወጣ ወጪም የፋይናንስ ምንጭ 1900 በመጠቀም የሚመዘገብ ሆኖ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በወጣዉ ወጪ ልክ በተጨማሪ በጀት የሚመዘገብ ይሆናል፣

15.2. ከመንግስት ግምጃ ቤት የሚመደብ በጀት በ1800 የፋይናንስ ምንጭ ተመዝግቦ የወጪ ሂሳብ መደቡ በተፈቀደበት ፕሮግራም እና የወጪ ሂሳብ ኮድ የሚመዘገብ ይሆናል፣

15.3. የዉጭ ዕርዳታ እና ብድርም በስምምነት ሰነዱ ላይ በተገለጸዉ የፋይናንስ ምንጭ እና የወጪ ሂሳብ መደብ በመከተል ወጪዉ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡

16. **የወጪ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ**

16.1. የግዥ ሂሳብ ሲወራረድ በደጋፊነት መቅረብ ያለበት ደጋፊ ሠነዶች የግዥ መጠየቂያ፣ የግዥ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤ፣ አቅራቢው የሰጠው ደረሰኝ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) እና ዊዝ ሆልዲንግ (Withholding) ታክስ የተቀነሰበት ደረሰኝ ናቸው፤

16.2. የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) እና ዊዝሆልዲንግ (Withholding) ታክስ መሰብሰቢያ ደረሰኞችን ከገንዘብ ሚኒስቴር ለዚሁ ተግባር ጠይቀው በመውሰድ ሥራ ላይ ይውላል፤

16.3. የጥቃቅን ሥራ ማስኬጃ ወጪ (Petty cash)፡- ለጥቃቅን ሥራ ማስኬጃ እንደ ነዳጅ፣ ውሎአበል እና ሌሎች አስቸኳይ እና አነስተኛ ወጪዎች የሚውል እስከ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ/ ብር ድረስ በካዝና በገንዘብ ያዥ ኃላፊነት ይንቀሳቀሳል፤

16.4. በአንድ የክፍያ መጠየቂያ ከካዝና ወጪ የሚሆን ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ) የማይበልጥ ይሆናል፤ ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ) በላይ የሚፈፀም ክፍያ በቼክና በባንክ ዝውውር የሚፈጸም ይሆናል፤

16.5. ለተለያዩ አገልግሎቶችና ዕቃዎች ግዥ ክፍያ ሲፈፀም የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የሚደረግ ታክስ በተዘጋጀው የታክስ አሰባሰብ ሕግ መሠረት ተግባራዊ ይደረጋል፤

16.6. የወጪ ማስመስከሪያ ቫውቸሮች ለዚሁ አገልግሎት ተለይቶ ለመደበኛ ከሚገዛው ውስጥ የተወሰኑ ቫውቸሮቹን ለይቶ በመውሰድ የሚጠቀም ይሆናል፤

16.7. የወጪ ሂሳብ ኮድ በመደበኛው በ IBEX ወይም IFMIS የአሠራር ሥርዓት የተዘረጋውን አርእስት የሚከተል ይሆናል፤

# ክፍል አራት

# የግዥ፤ ንብረት አያያዝና አወጋገድ

17. **የግዥ አፈፃፀም**

17.1. ወረርሽኙ ጊዜ የማይሰጥ አጣዳፊ፣ የሰውን ህይወት የሚቀጥፍ እና በፍጥነት የሚሰራጭ በመሆኑ ይህንኑ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ለአስቸኳይ ሥራዎች የሚፈለጉ ዕቃዎችን ለመግዛት በመንግስት ግዥ አዋጅና መመሪያ ላይ ለእንደዚህ ዓይነት አጣዳፊ አደጋዎች ግዥዎች ለመፈጸም በተደነገገው  መሰረት ግዥው ሊፈጸም ይችላል፤

18. የንብረት ገቢና ወጪ አያያዝ

18.1. ለወረርሽኝ አገልግሎት የሚገዛ ዕቃ ከፋብሪካ ወይም ከአከፋፋይ ድርጅቶች በጥቅል የሚገዛና ወደ ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በዚያው በኩል የሚሰራጭ በሚሆንበት ጊዜ ንብረቱ ከተላከላቸው ክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች ንብረቱ ለመድረሱ የሚሰጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ  አስፈጻሚው መስሪያ ቤት ሲደርሰው ምዝገባውን ያከናውናል፤

18.2. ለፌዴራል አገልግሎት ግዥ የተፈፀመ ንብረት በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል -19) አስፈጻሚው መስሪያ ቤት በሚያዘጋጀው ስቶር (የንብረት መጋዘን) ገቢ ያደርጋል፤

18.3. የንብረት ወጪ ከሚመለከተው አካል ትዕዛዝ ሲሰጠው በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) መሠረት ለሚመለከተው አካል ይሰጣል፤ ይህንኑ ምዝገባ ያካሂዳል፤

19. የንብረት አወጋገድ ሥርዓት

19.1. ወረርሽኙ በቁጥጥር ሥር መዋሉ በብሔራዊ ኮሚቴ መግለጫ ከተሰጠ በኋላ ሥራ ላይ የማይውሉ ዕቃዎች በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ይወገዳሉ፤

# ክፍል አምስት

# የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ

20. **የሂሳብ አያያዝ ዘዴ**

20.1. የፈንዱ ሂሳብ የመደበኛውን በጀት የ IBEX ወይም  IFMIS የሂሳብ አሰራር ሥርዓትን ይከተላል፤

20.2. የሂሳብ አወቃቀር

ሀ. የአገር ውስጥ እርዳታ የገቢ ሂሳብ በኮድ 1483 በመጠቀም የአገር ውስጥ እርዳታ ተብሎ ይመዘገባል፤

ለ. የውጭ አገር እርዳታ ሲገኝ የዕርዳታ ሰጪውን የገቢ ኮድ በመጠቀም ይመዘገባል፤

ሐ. ከዲያስፖራ የሚገኝ (ዶላር) ዕርዳታ የገቢ ሂሳብ ኮድ 1489 በመጠቀም ይመዘገባል፤

መ. የወጪ ሂሳብ እና ሌሎች መደበኛ /Natural Accounts/ መደበኛውን የ IBEX ወይም IFMIS የሂሳብ አሰራር ስርዓት በመጠቀም ይመዘገባል፤

20.3. የሂሳብ መዝገብና አያያዝ

ሀ. የሂሳብ መዝገብ ለዚሁ ለኮሮና ቫይረስ (COVID-19) መቆጣጠሪያና መከላከያ ከመንግስት የተመደበ በጀት፣ የአገር ዉስጥ እርዳታ እንዲሁም የዉጭ ዕርዳታ እና ብድር ለየብቻ በየፋይናንስ ምንጩ የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (Transaction Register) በ IBEX ወይም IFMIS በመክፈት ይያዛል፤

ለ. የሂሳብ ሌጀሮችም በእያንዳንዱ የሂሳብ ኮድ ጠቅላላ እና ተቀጽላ ሌጀሮችን በማዘጋጀት ይያዛል፤

ሐ. በየወሩ የባንክ ማስታረቂያ ይዘጋጃል፤

መ. በየእለቱ የሳጥን ሂሳብ ቆጠራ ይደረጋል፤

20.4. የሂሳብ ሪፖርት ይዘት እና የማቅረቢያ ጊዜ

20.4.1. የሂሳብ ሪፖርት ይዘቱ የሚከተሉትን ያጠቃልላል

ሀ. የገቢ ሂሳብ ሪፖርት

ለ. የወጪ ሂሳብ ሪፖርት

ሐ. የገንዘብ ዝውውር ሪፖርት (ከመንግስት የሚመደብ ድጎማ በጀት)

መ. የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት

ሠ. የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት

ረ. የሂሳብ ማመዛዘኛ ሪፖርት

ሰ. የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ከነ ባንክ መግለጫዉ

ሸ. የሣጥን ቆጠራ ሪፖርት

20.4.2. የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜ

ሀ. አስፈጻሚው መስሪያ ቤት የሂሳብ ሪፖርቱን በየሶስት ወሩ ለገንዘብ ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖረት ያቀርባል፤

# ክፍል ስድስት

# የቁጥጥር እና ኦዲት ሥርዓት

21.የቁጥጥር እና ኦዲት

21.1. አላቂ፣ ቋሚ እና በአደራ የተሰጡ ንብረቶቹ በየሶስት ወሩ ቆጠራ እየተደረገ ከወጪ ቀሪ ሚዛኑ ሪፖርት እየተዘጋጀ የሚቀርብና በመጨረሻም ኦዲት ስለምደረግ በስርዓት ተመዝግቦ ይቀመጣል፤

21.2. የሂሳብ መዛግብቶች በትክክል እንዲያዝ በማድረግ በአስፈጻሚ መስሪያ ቤቶች በኩል በውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት የሚደረግ ይሆናል፤

21.3. ወረርሽኙ በቁጥጥር ስር መዋሉ በብሔራዊ ኮሚቴ ለሕዝብ ከተገለጸበት ዕለት አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ ይቀርባል፤

# ክፍል ሰባት

# ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

22. ይህ መመሪያ ከሚያዝያ 15 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፤

አዲስ አበባ

አህመድ ሽዴ

ገንዘብ ሚኒስትር